" ነፍስ አጥፍተህም ሆነ በሌላ የተለያየ ምክንያት በየሜካው በሽፍትነት የምትኖር የአገሬ ሕዝብ ሆይ ከዛሬ ጀምሮ ምህረት ስለተደረገልህ ከደመኛህ ጋር እየታረቅህ ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለህ በሰላም ኑር" የሚል የምህረት አዋጅ ባገራችን በተለያየ ጊዜ በተለይም መንግስት ሲለወጥ ይታወጃል ። ይህ የምህረት አዋጅ በአገሪቷ ላይ ሁሉን ማድረግ የሚችል አቅም ባለው አካል ቢታወጅም ተገባራዊ ለመሆን ግን የራስን ጥረት ይጠይቃል ፣ ደም ከተቃቡት ጋር መታረቅን።

ሁሉን የሚችል የእግዚአብሔር ምህረት ግን ለየት ይላል ፣ ተደብቀን ላንደበቅ ስንሸሽግ ያለንበት ሳያውቅ ቀርቶ ሳየሆን እራሳችን ለራሳችን ጠፍተን እንዳንቀር ሊያነቃን ወዴት ነህ ይላል፣ የማያዛልቅን መፍትሄ ቅጠልን አውልቆ ደም በማፍሰስ ቁርበት ያለብስና ተስፋ ሰጥቶ ቀን ይቀጥራል ፣ ተበዳዩ እርሱ ሆኖ እያለ የተገላቢጦሽ ካሳ ክሶ ይቅር ሊል ፣ ዋጋ ከፍሎ ገዝቦ ሊያደርገን እና የማይገባንን የተገባን እንድንሆን ያልተገባውን መንገድ ይሄዳል ። አቤት ምህረቱ ! አቤት ፍቅሩ እንጂ ሌላ ምን ይባላል።

እግዚአብሔር አብ ለእኛ ያለውን ፍቅሩን ልጁን ስለ እኛ አሳልፎ በመስጠት እና ስለ እኛ ያለውም እርህራሄ በልጁ ላይ በመጨከን ገለጠው ። ጌታ ኢየሱስም ሊያልፍበት ያለው መከራ ወዙ በምድር ላይ እንደ ደም ነጠብጣብ እየተንጠባጠበ "አባት ሆይ ብትፈቅድስ ይህቺ ጽዋ ከእኔ ትለፍ ........" በማለት እንዲፀልይ ቢያደርገውም ያባቱ ፈቃድ ግን ስለ እኛ ሃጥያት ደሙን በማፍሰስ ዋጋ እንዲከፍል ነበር እና ያንን ለማድረግ ጨከነ ።እራሱን ስለ እኛ አሳልፎ በመስጠት የማይገባውን ሞት በመሞት በመስቀል ጣር ወለደን።

ይህን የሚገርም የፍቅር ስጦታ ተቀብለዋል? በጌታ ኢየሱስ የመስቀሉ ስራ እዳዎ በሙሉ እንደተሰረዘ አምነው የህን ሰጦታ የግሎ አድርገዋል ? ይህን እርምጃ ከወሰዱ የምስራች ! በዮሐንስ ወንጌል ምዕ8 ቁ 36 ላይ "እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ" ይላል ስለዚህ በነፃነት ይመላለሱ ።

እዳ ያለበት ሰው በመሸማቀቅ ቀና ብሎ ካለመሄዱ የተነሳ ጎብጦ፣ ባድርግ አታድርግ ሕግ ተሸማቆ የኖረ ማንነት ይህን የነፃነት ሕይወት ለመኖር ሲጀምሩ ብቅ ጥልቅ እያለ ማስቸገሩ መቼም አይቀሬ ነው ። ለዛም ነው ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 11 ቁ28-29 ላይ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ" በማለት የእረፍትን ሕይወት ቃል ከገባልን በኋላ እንዴት ደግሞ መኖር እንዳለብን ሊያሳየን "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ" ያለን ፣ መቼም አርሶ የማያውቅ በሬ ጥሩ ከሚያርስ በሬ ጋር አደል የሚጠመድ። አደራረግን እንዲለምድ።

ታዲያ ምን እናድርግ?

- በገላቲያ 5፡ 1 ላይ "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" ይላል ነፃ ያወጣን ጌታ በቂ ከበቂም በላይ ነው ።ስለዚህ ነፃ ለመውጣት የምንታገል ነፃ አውጪዎች ሳንሆን ነፃነታችንን በማወቅ እንመላለስ፣ በመፍጨርጨር ሳይሆን ልጅነት የሚገኘው በመወለድ ነው እና የምናደርገው ለመሆን ሳይሆን ስለሆን ይሁን"
- በሐዋሪያት ስራ 26፡16 "ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና" ይላል ጌታ ከወደቅንበት ሲያነሳን ፣ ከጠፋንበት ፈልጎ ሲያገኘን ምስክሮቹ እንድንሆን ነው። በረከቱ ከኛ አልፎ ለሌሎች እነዲተርፍ ነው ። የጌታን ምህረት እና ቸርነት ስናወራ አንደኛ በእምነታችን

እየጠነከርን እንሄዳለን ሁለተኛ ለሌሎች የመዳኛ ምክንያት እንሆናለን ደግሞም መናገራችን ይለየናል ።

- በ1ኛ ጴጥሮስ ም2 ቁ2-3 ላይ “ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ” በማለት ሐዋሪያው ጴጥሮስ ቃሉን ላለማንበብ የምናቀርበው ምክንያት እንዳይኖረን በማድረግ አጥሮብን ሰበባችንን ሁሉ እንዲህ በማለት አመከኖብናል፤ ቃሉ ተንኮል የሌለበት ንጹህ እንደሆነ ፣ ህጻን ሆኖ መቅረት አለመሻታችን እና ለማደጋችን ደግሞ አስፈላጊና አማራጭ ሌላ የሌለ መሆኑ፣ የጌታን ቸርነት መለማመዳችንንም ደግሞ ምስክር ጠቅሶብናል ስለዚህም በግል ቃሉን የምናጠናበት የጥሞና ጊዜ ሊኖረን ይገባል።
- 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:17-18 “ሳታቋርጡ ፀልዩ በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና” ይላል ፣ ፀሎት በተለምዶ እንደምናደርገው መድገም ሳይሆን ንግግር ነው ። ንግግር ደግሞ በሁለት አቅጣጫ ነው የሚሆነውና መናገርን ጥያቄ መደርደር ብቻ ሳየሆን ማዳመጥንም እንለማመድ። በማመስገን በማወደስ እና በማምለክ እፊቱ የምንሆንበትን ጊዜ በግላችን እነዲኖረን ሁኔታዎችን እናመቻች ፣ የግል መሰዊያችንን ሳንሰራና በዛም ላይ መስዋእትን ማቅረብ ሳንለማመድ (የግል የፀሎት ጊዜ ሳይኖረን) በሕብረት የፀሎት ፕሮግራሞችን መሳተፍ ከሕይወት ይልቅ ወደ ሃይማኖት ሊወስደን ስለሚችል ጥንቃቄ እንውሰድ።
- በመዝሙር 133 ቁ1 ላይ “ወንድሞች በሕብረት ቢቀመጡ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው” ይላል ፣እግዚአብሔር አምላክ በቃሉ ውስጥ ስለ ሕብረት ብዙ ይላል በግል በቤታችን የምናደርገው የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናትና ፀሎት አስፈላጊ እንደሆነው ሁሉ ሕብረትም ለክርስትና እድገታችን ወሳኝነት አለው።በሕብረት ውስጥ እናድጋለን፣ ከጠላት ጥቃት እንከለላለን ፣ እንበረታታለን ፣እንተናነፃለን፣ እንሰራለን ፣በዓለም ያሉ ሰዎች የጌታ መሆናችንን የሚለዩበት ዋነኛው መታወቂያችን የሆነው “ፍቅር” መገለጫው በሕብረት ውስጥ ነው። እግዚአብሔርንም የመውደዳችን መለኪያው ሐዋሪያው ዮሃንስ በ1ኛ መልዕክቱ ላይ “ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?” በማለት ያስቀመጠልን ይህ መስፈርት የሚተገበረው እኮ በዚሁ በሕብረት ውስጥ ነው። ስለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ወደ ዕብራዊያን ሰዎች በፃፈው መልዕክቱ “በአንዳንዶች ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ” የሚለን ስለዚህ ሕብረት አስፈላጊያችን ነው።
- ጌታ ለቤተክርስቲያን የሰጣት ተልዕኮ አህዛብን በምስራቹ ቃል መድረስ ፣ ማጥመቅ ፣ የጌታ ትዕዛዛት ሁሉ እንዲጠብቁ ማስተማር እና ደቀ መዝሙር ማድረግ ነው። የምስራቹን ቃል ሰምተን ካመን የውሃን ጥምቀትን እንውሰድ ምክኒያቱም በዋናነት የጌታ ትእዛዝ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሐዋሪያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በፃፈው መልዕክቱ “እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።” ሲለን በቆላስይስ ላይ ደግሞ “በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።” ይለናል ስለዚህ ትእዛዙን በመፈጸም ይህንን መንፈሳዊ ልምምድ እንለማመድ።
- በሁለተኛ ደረጃ ትእዛዙን ሁሉ እንድንጠብቅ ነው። ትእዛዙን ደግሞ መጠበቅ የምንችለው በአድርግ አታድርግ ሕግ ተደንግጎብን ሳይሆን በመማር ነው። መማር ያሳውቃል ፣ ማወቅ ደግሞ አስተሳሰብን ይለውጣል የተለወጠ አዕምሮ ደግሞ እንደ ነበርን እንድንቀጥል ነፃነትን ባለመስጠት በተለወጠ ሕይወት እንድንመላለስ ያደርገናል ፣ ስለዚህ የቤተክርስቲያን አደራ ማስተማር ሲሆን እኛ ደግሞ በተዘጋጀልን ገበታ ላይ በመገኘት መማር አለብን ይህ ካልሆነ ግን የሚጠበቅብንን ሕይወት በተገቢው መልኩ መኖር የማንችል እንዲሁ የቤተክርስቲያን ደንበኛ ብቻ ሆኖ መቅረት አለ ፣ ያ ደግሞ የጌታን ትእዛዝ ሙሉ አያደርገውም ምክኒያቱም የታላቁ ተልዕኮ ግቡ የምዕመናንን ቁጥር ማበራከት ሳየሆን ደቀ መዝሙርን ማፍራት ነው። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ለቲቶ በፃፈው መልዕክቱ

“ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል” በማለት ይህ የተገለጠው ፀጋ ባለቤት ያለው መሆኑ ፣ የእርሱ ያልሆነውን የሚያስከድ እንዲሁም ለሰው ሁሉ የሚሆን የተትረፈረፈ እና በቂ የሆነ እንደሆነ ካስረገጠ በኋላ የተባረከውን ተስፋ ያም የጌታን ዳግም መምጣት መጠባበቅ እንዳለብን ያሳስበናል መቼም የከበረን እንግዳ እየተጠባበቁ መዘረክረክ አማይታሰብ ነው ፣ ግን ቢሆንም አጭበርባሪ ጠላት አለና በእርሱ ውሸት ተታለን እንዳንዘናጋ ዘዴው ራስን መግዛት ፣ መንገዱ የጽድቅ የምንመስለው ደግሞ አገሌን ወይም አገሊትን ሳየሆን እግዚአብሔርን ራሱን እንደሆነ የምንኖርበትም ዘመን በቀጠሮ የነገ ሳየሆን ዛሬ እንደሆነ የሚያሳስብ እና የሚያስተምር መልካም መምህር እንዳለን ከነገረን በኋላ ጌታ ኢየሱስ እራሱን አሳልፎ የሰጠበትን አላማ ሲገልጥ ደግሞ “መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።” ይለናል ስለዚህ

ዮሃንስ በ፤ኛ መልዕክቱ

“የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።
ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።
በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል”